በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ.200968

ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡.......አቶ ሙሉጌታ ኃ/ማርያም- ቀርበዋል

ተጠሪ፡............አቶ ነጋሽ ያደቴ- ተወካይ አባይነህ ነጋሽ ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ይህ የእርሻ መሬት የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.251106 ጥቅምት 26 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ክልል ዉስጥ ግብር እየገበርኩበት ያለዉን ሁለት ቀርጥ (አዋሳኝ በመጥቀስ) የእርሻ መሬት ይዞታዬን የካቲት ወር 1989 ዓ.ም ባደረግነዉ ዉል ለጊዜያዊ ችግሬ መዋያ ብር 7000 (ሰባት ሺህ) ከተከሳሽ ተቀብዬ መሬቱን ለተከሳሽ የሰጠሁ፣ ገንዘቡን ስመልስለት ደግሞ መሬቱን ሊመልስልኝ የተስማመን ሲሆን፣ ተከሳሽ ገንዘቡን ተቀብሎኝ መሬቱን እንዲያስረክበኝ ፈቃደኛ ስላልሆነ፣ ተከሳሽ ገንዘቡን ተቀብሎኝ የእርሻ መሬቱን እንዲያስረክበኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ ክርክር ከሳሽ በዚህ መሬት መብትና ጥቅም የለዉም፤ ተከሳሽ ይህን መሬት በዉል አልተቀብኩም፤ መሬቱን በዉል ተቀብለአል የሚባል ከሆነ ዉሉ ተደርጓል ከተባለ ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ ከ21 ዓመታት በላይ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመመርር ባሳለፈዉ ዉሳኔ ከሳሽ የግብር ደረሳኝ ያቀረበ በመሆኑ በመሬቱ ላይ መብትና ጥቅም አለዉ፤ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ተከሳሽ መሬቱን ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ መያዙን ገልጸዉ የተከራከሩ በመሆኑ ይህ ጊዜ ሲሰላ ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ዉሳኔ አንጻር በ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ሊታገድ ይገባል በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔና ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ጥር 7 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች ግብር የሚገብርበትን አከራከሪዉን የእርሻ መሬት ይዞታዬን ከተጠሪ ገንዘብ ወስጀ የሰጠሁት በመሆኑ አመልካች ከተጠሪ የወሰድኩትን ገንዘብ ስመልስለት ይዞታዉን ሊመልስልኝ ተስማመን ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም፤ አመልካች መሬቱን ለተጠሪ የሰጠሁት በወለድ አግድ ዉል መልስ በመሆኑ የባለይዞታዉ መብት በይርጋ ሊቋረጥ የማይችል እና አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ የመፋለም ክርክር ስለሆነ ጉዳዩ በይርጋ ዉድቅ ሊሆን አይገባም ተብሎ የሥር ፍ/ቤት ብይን ተሽሮ ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክር ገብተን እንዲንከራከር እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ249/2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ምንም ዓይነት የመያዣ ዉል አልፈጸምኩም፣ የመያዣ ዉል አለ ቢባል እንኳን ክስ የቀረበዉ ከ21 ዓመት በላይ የሆነዉ ስለሆነ ክሱ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነዉ መባሉ የሚነቀፍበት አግባብ የለም፤ አመልካች ያቀረበዉ ክስ ዉልን የሚመለከት እንጂ የመፋለም አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ፤በዚህ ጉዳይ ተገቢ የሆነ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመያዝ ዉሳኔ የተሰጠ መሆን አለመሆኑን? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረግነዉ ዉል ለክርክር መነሻ የሆነዉን ይዞታ ለተጠሪ የሰጡት ከተጠሪ ገንዘብ ተቀብዬ ሲሆን ገንዘቡን ስመልስለት ተጠሪ ደግሞ መሬቱን ሊመልስኝ ተስማምተን ስለሆነ አሁን ገንዘቡን ወስዶ መሬቱን እንዲያስረክበኝ የሚል ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች አከራከሪዉን መሬት ለተጠሪ ሰጠሁት የሚለዉ በዉል ምክንያት መሆኑን ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር ከአመልካች ጋር ምንም ዓይነት ዉል አላደረግኩኝም፤ ዉሉ አለ ቢባል እንኳን ከ21 ዓመት በላይ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት

ተከራክሯል፡፡ ስለሆነም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በይርጋ መቃወሚያ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት ተገቢዉን ጭብጥ በመለየት በመያዝ በማጣራት አግባብነት ካለዉ ሕግ አንጻር መርምሮ መወሰንን ይጠይቃል፡፡

እንደሚታወቀዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 (1) መሰረት ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ አስቀድሞ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ ለቀረበለትና ማናቸዉም ተከራካሪ ወገን ላቀረበዉ መቃወሚያ ዉሳኔ መስጠት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ፍ/ቤቱም በቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ተቀብሎ ሌላዉ ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ ዉሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የሚገምተዉ ማስረጃ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ይሰጣል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.245 (1) ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ከዚህ የህግ ደንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለዉ በቀረበዉ የመጀመሪያ መቃወሚያ ላይ አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ፍ/ቤት ማስረጃ በመስማት በመጣራት ዉሳኔ መስጠት እንደሚገባዉ ያስገነዝባል፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር አከራካሪዉን መሬት ለተጠሪ በዉል ሰጥቻለሁኝ ያለዉ ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩሉ ደግሞ ከአመልካች ጋር ምንም ዓይነት ዉል አላደረግንም፣ ዉል አለ ቢባል እንኳን በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ክዳዉ ተከራክሯል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገነዉ ዉል መሬቱን ሰጥቻለሁ ያለዉን፣ በተጠሪ በኩል የተካደ ስለሆነ፣ በግራ ቀኙ መካከል አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ተጣርቶ ነጥሮ መዉጣት ያለበት ጭብጥ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነዉን መሬት በዉል ለተጠሪ ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? አመልካች መሬቱን በዉል ለተጠሪ ሰጥቷል የሚባል ከሆነ የአመልካች ክስ በይርጋ የሚታገድ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙን ካከራከረዉ ከዉል አንጻር ጭብጥ መስርቶ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማጣራት በሕጉ አግባብ ተገቢ ነዉ ያሉትን ዉሳኔ ማሳለፍ ይገባቸዉ ነበር፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር አስመልክቶ ከዉል አንጻር ሳይመርምሩ ክሱን ዉድቅ ማድረጋቸዉ የህግ ድጋፍ የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት በማድረግ ከዉል አንጻር ጭብጥ በመመስረት አጣርቶ አለመወሰናቸዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.97708 በ15/4/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.251106 በ26/2/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነዉን የመሬት ይዞታ በክሱ በተጠቀሰዉ አግባብ በዉል ለተጠሪ ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? አመልካች መሬቱን በዉል ለተጠሪ ሰጥቷል የሚባል ከሆነ የአመልካች ክስ በይርጋ የሚታገድ ነዉ

ወይስ አይደለም? የሚለዉን ከግራ ቀኙ የሚቀርብ ማስረጃ ካለ በመመርመር፣ አግባብነት ባለዉ ማስረጃም በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ብይን እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. ይህ ዉሳኔ ታህሳስ 4 ቀን 2014 ዓ.ም ተነቧል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

**ማ/አ** **የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ.መ.ቁ.200968

ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም

**ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደምከተለው አስቀምጫለሁ**

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ባቀረበው ክስ ለአሁን ተጠሪ የእርሻ መሬት ይዞታዬን ገንዘብ ተቀብዬው መሬቱን እንዲጠቀምበት ያስረከብኩትና ገንዘቡን ስመልስለት መሬቱን እንዲመልስልኝ (ወለድ አግድ) ተስማምተን በ1989 ዓ/ም የእርሻ መሬቴን የሰጠሁት ሲሆን አሁን ገንዘቡን ወስዶ መሬቴን እንዲመልስልኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆኑ መሬቴን እንዲለቅልኝ ሲል የጠየቀ ሲሆን የአሁን ተጠሪም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክሱ በይርጋ ውድቅ እንዲሆንለት ጠይቆ በፍሬ ነገሩ ላይም መልስ ሰጥቷል፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 69302 ላይ በሰጠው ውሳኔ አንድ የእርሻ መሬት ባለይዞታ በመሬት የመጠቀም መብት ለማስከበር በ10 ዓመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ ክሱ ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በሰጠው መሰረት የአሁን አመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የቀረበውን ዳኝነትና የእርሻ መሬት ይዞታን በተመለከተ ከህገ መንግስቱ ጀምሮ ያሉትን ህጎች እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም እንዲሁም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ም/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ካለመገንዘብ የደረሱበት ድምዳሜ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይሄውም ማንኛውም በእርሻ መሬት ላይ የሚደረጉ ውሎችን እንደማንኛውም የግል ንብረት ላይ የሚደረጉ ውሎች በፍ/ብ/ህግ የውል ድንጋጌዎች ሲዳኙ ይታያል፡፡ በፍ/ብ/ህጋችን ላይ ስለመሬት የተደነገጉት ድንጋጌዎች መሬትን በግል ንብረትነት እይታ መነሻነት ተወስዶ የተቀመጡ ድንጋጌዎች ሲሆኑ የፍ/ብ/ህግ 1173፣ 1178፣ 1179 እና ሌሎቹም ድንጋጌዎች ይህንኑ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ይሁንና ከደርግ መንግስት ጀምሮ በመሬት ላይ ያለው የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ የተለወጠና መሬት የህዝብና የመንግስት ሆኖ ባለይዞታው ከመሬት ባለቤትነት ያነሰ መብት ያለው መሆኑ ማንኛውም ሰው ግንዛቤ የለውም ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 40(3) የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው ሲል ደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህ ሆኖ ባለበት የእርሻ መሬት ላይ የሚደረጉ ክርክሮችን በተመለከተ ህገ መንግስቱን መሰረት በማድረግ የወጡ ህጎች እያሉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ም/ቤት ውሳኔዎች እያሉ በፍ/ብ/ህጉ ድንጋጌዎች እይታ መዳኘት ተገቢነት የሌለውና የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ይሆናል፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 40(4)

የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ አፈጻጸሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል ሲል ደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የእርሻ መሬት የሚተላለፈው ባለይዞታ ለቤተሰቡ አባላት በውርስና በስጦታ ልያስተላልፍ የሚችል ሲሆን ከባለይዞታው የቤተሰብ አባለት ውጪ የሚደረጉ የእርሻ መሬት ማስተላለፍ ጉዳይ የእርሻ መሬት ባለይዞታውን ከይዞታው የሚያፈናቅለው በመሆኑ ህገ መንግስቱን የሚጻረር ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት በተለያዩ የእርሻ መሬት ክርክሮች ላይ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔና ሌሎቹንም መመልከት ይቻላል፡፡ እነዚህ ውሳኔዎች የእርሻ መሬት በተመለከተ በሚነሱ ክርክሮች የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጨምሮ የሚሰጡት ውሳኔዎች ከህገ መንግስቱ ጋር የሚጻረሩ በመሆኑ ህገ መንግስቱን በመተርጎም የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት የሰጣቸው ውሳኔዎች ናቸው፡፡ ከእርሻ መሬት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች ይርጋን በተመለከተ የእርሻ መሬት ይዞታ በህገ ወጥ መንገድ ተላልፎ የተገኛ እንደሆነ ክሱ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና ሌሎችም ውሳኔዎች በቂና አስገዳጅ ማሳያዎች ናቸው፡፡ መሬት በህጋዊ መንገድ የተላለፈ ስለመሆን አለመሆኑና በህገ ወጥ መንገድ የተላለፈ ስለመሆኑ የኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 40(4) ባስቀመጠው ድንጋጌ መሰረት የየክልሎቹ የገጠር መሬትን ለማስተዳደር የወጡት አዋጆች በግልጽ ደንግገው የሚገኙ ሲሆን የእርሻ መሬት በህጋዊ መንገድ የሚገኘው ከመንግስት በምሬት ስገኝ፣ ከመሬት ባለይዞታው በውርስ ወይም በስጦታ ለቤተሰቡ ሲተላለፍ ሲሆን ከዚህ ውጪ የሚደረጉ የእርሻ መሬት ማስተላለፍ ሁሉ ህገ ወጥ የሚሆኑ ናቸው፡፡ የቤተሰብ አባል ማለት ምን እንደሆነ እነዚሁ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጆች ደንግገው ይገኛሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 179827 ላይ በሰጠው ውሳኔ እንድ ሰው የገጠር መሬት በህጋዊ መንገድ የያዘ ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ጊዜ ድረስ መሬቱን የያዘው በህገ ወጥ መንገድ መሆኑ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያን በስነ ስረዓት መቃወሚያነት ሊያነሳ የማይችል ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ የፌደራል እና የየክልሎቹን የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጆችንም ማየት ይቻላል፡፡ ሌላው የኢፌዴሪ ፌደሬሽን ም/ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔም ይርጋን በተመለከተ ተጠሪ ከአመልካች ላይ ለ50 ዓመት የእርሻ መሬት ተከራይቻለሁ በማለት ያቀረበው ክርክር የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ድንጋጌን የሚቃረን ከአዋጁ ውጪ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥቼበታለሁ በማለቱ ብቻ ባለይዞታው ይዞታውን እንዲያጣ እና ከይዞታው እንዲፈናቀል የሚያደርገው በመሆኑና የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(4) የሚቃረን ስለሆነ ተፈጻሚነት የለውም ሲል ውሳኔ ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ/ቁጥር 79394 ላይ በሰጠው ውሳኔ በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ ወይም የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ ከመነሻውም ውጤት የሌለውና ፈራሽ መሆኑን፣ የውሉ መሰረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈጻሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት በዚህ ጉዳይ 1. ክሱ የአሁን አመልካች በወለድ አግድ ውል የእርሻ መሬቴን ለተጠሪ ሰጥቼዋለሁ ሲል ያቀረበውን ዳኝነት ወለድ አግድ ህገ ወጥ የሆነ በእርሻ መሬት ላይ የተደረገ ውል መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ እየታወቀ ክሱን በይርጋ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ 2. የኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 40(3 እና 4) መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የህዝብና የመንግስት ሀብት መሆኑንና ባለይዞታው ከይዞታው ያለመነቀል መብት ያላቸው ስለመሆኑ ተደንግጎ እያለ በህገ ወጥ መንገድ የሚተላለፉ የእርሻ መሬቶች ሁሉ

በይርጋ የማይታገዱ ስለመሆኑ የፌደሬሽን ም/ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሰጥተውበት እያለ ይህ ሁሉ ታልፎ የአሁን አመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ ይህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው እላለሁ፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካችን ክስ በይርጋ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የአሁን ተጠሪ ክስ የቀረበበትን የመሬት ይዞታ ከአሁን አመልካች አልተቀበልኩትም የሚል ክርክር ያለው በመሆኑ በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን መመለስ ሲገባ ህገ ወጥ በሆነ የወለድ አገድ ውል ላይ በመመስረት ክሱ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆን አለመሆኑ ተጣርቶ እንዲወሰን ተብሎ መመለሱ ህጉን ያልተከተለና ካለአግባብ ተከራካሪ ወገኖችን ላልተፈለገ ወጪና የጊዜ ብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ተገቢ አይደለም እላለሁ፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት